# ለተማሪ ፡ ለመምህር፣ የዕውቀት፡ ዓመት፡ ይሁን ።

በአኔ ዘመን መስከረም አስራ ስምንት ቀን ፤ትምህርት ቤት ሲከፈት፤ በክፍል ተቀምጠን፣ በመስክ ላይ ወጥተን ፣ በመንገድ ላይ ሆነን ፣ በገበያ ሥፍራ ፣ከቤትም ስንገባ፤

አትማርም ወይ? አትማርም ወይ?
ቆለጅ መቸርቸር ይሻልሃል ወይ?

ነበር መዝሙራችን። በትንሿ ከተማችን የየመን ተወላጅ የሆኑ አረቦች ሱቅ ከፍተው ይነግዳሉ።በተጨማሪም ከአካባቢው ሌጦና ከርቤ እየገዙ በሳምንት ሦስቴ መጥቶ በሚያርፈው ዲሲ ሦስት አይሮፕላን በአዲስ አበባ በኩል ወደውጭ ሃገር ይልካሉ።ስለዚህ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ብዙ ወጣቶች ቆለጅና ከርቤ ንግድ ላይ ይሰማራሉ።ከአባቢውና ራቅ ብሎ ከቆላው ከርቤና ሌጦ አቅራቢዎች ላይ እየገዙ ለአረቦች ይሸጣሉ። አንዳንዶቹ ገንዘቡ ይጥማቸውና ወደ ትምህርት ቤት አይመለሱም። መምህራኑም ይህንን ስለሚያውቁ፣ ሆን ብለው ነበር ይህችን መዝሙር እንድንዘምር ያስተማሩን። ፈረጆችም ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች የሚሏቸው አላቸው።' do not let the green grass fool you.' አረጓዴው ሣር እንዳያታልልህ ፤ አረጓዴው ሣር ብር መሆኑ ነው። ዛሬ አረጓዴ ሆኖ ቢታይህ ነገ ደራቂ ነው ፤ ዕውቀት ግን አይደርቅም ማለታቸው ነው።በተጨማሪም ዕውቀት ሁለተናዊ ነፃነት ነው። ይህንን የሚያራምዱ መምህራን ደግሞ Teachers are Angels disguised human beings.መምህራን በሰው መልክ የቀረቡ መልዓክት ናቸው። አዎን ያቺን መዝሙር ያስተማሩን መምህራን መልዓክት ነበሩ።

የሃገራችን ሰው እንደማንኛውም የዓለም ሕዝብ ከሚተነፍሰው አየር ከሚመገበው ምግብና ከሚለብሰው ልብስ ቀጥሎ ለሕይወቱ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ያምናል። ሆኖም እምነቱን ዕውን ለማድረግ ብዙ መሰናክሎች አሉበት። መሰናክሎቹን በዚህ አጭር ጹሑፍ ልመልሰው አልችልም። የትምህርት ፍቅር የቱን ያህል በሕዝባችን ልብ ውስጥ እንደሰረጸ ግን በዚች አጭር ምሳሌ ለማሳየት ልሞክር።

በግርማቸው ተክለሃዋሪያት የተደረሰውን 'ቴወድሮስ' የሚለውን መጽሐፍ በድራማ መልክ ለወላጆች ቀን ለማቅረብ የትያትር ክለብ አላፊያችን መምህር ሐሳቡን አቀረበ። በደስታ ተቀበልነው። እኔም ተዋናይ የምሆንበትን ትዕይንት ሌት ጮክ ብዬ ሳጠና እናቴ ተኝታ ታዳምጥ ኖሯል። አንድ ቀን ዘመዶቻችን ከገጠር መጥተወ እኛ ቤት በወለሉ ላይ ቁርበት ተነጥፎላቸው አድረዋል። አናቴም በሌሊት ተነስታ ቡናውን አፍልታ ጎረቤቶች ተጠርተው ቡናው ቀርቦ የአንገት ለብስ መሰል ኮታ በትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ፤ እጣኑ ተጨሶ፣ የቁርሱ ዳቦው ተቆርሶ፣ እኔም ሐባዬን ዳቦዬ ይዤ ለመውጣት ስጠባበቅ እናቴ 'ያን ሰሞኑን ታነበው የነበረውን መጽሐፍ አንብብልን' አለችኝ። ለነገሩ እናቴ ኦሮመኛና አማርኛውን አቃላጥፋ እየተናገረች ሳድስና ሳልስ ፊደላትን በትክክል ማለት ይቸግራታል። 'መጠሐፉን' ነበር ያለችው። የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። በዚህ ዕድሜ መዓድ መቅረብ ፤እግርን አንፈራጦ ከአዋቂ ጋር ቡና መጠጣት፣ ሳያሰቡ መናገር፣ አውቃለሁ ብሎ ስለማያውቁት ነገር መቀባጠር አይፈቀድም። እናቴ ስለቴዎድሮስ ድራማ አንብብ ስትለኝ ደስታውን አልቻልኩትም። የሚያስደስታቸውን አውቀዋለሁ። ገጾችች ገልብጥ እያደረኩ ማንበቤን ቀጠልኩ።

ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፣
ዐርብ ዐርብ ያሸብራል ኢየሩስዓሌም።
የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል፤
የሚሉት ተረት ፣
በእርሶ ላይ ደረሰ ኢቴጌ ይረዱት።

የገብርዬን ፣ የተዋበችን፣ የራስ አሊን በመጨረሻዋ ሰዓት ቴዎድሮስ ጥይታቸውን ጠጥተው ሊሞቱ ሲሉ የታገሩትንና ማረፋቸውን አረዳኋቸው። ከመቀመጫዋ ተነስታ 'ይህን ነው ያልኩህ!' አለች እናቴ። ሴቶቹ እንባ ሲያቀሩ፤ ወንዶቹ ተቁነጠነጡ። ዝመዶቻችንም ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት እንደሚያስገቡ ፎክረው ሄዱ። አልቀረም ቢያንስ ከነሱ አካባቢ አስር የሚሆኑ ወጣቶች ትምህርት ቤት ገቡ። እናቴ አንኳ ያሰደሰታት የቴዎድሮስ ጅግንነት ነበር። ሆኖም ለአስር ልጆች መማር ምክንያት ሆነች። ነፍሷን ይማር።

በዚህ ወቅት መልካም የዕውቀት ዘመን የተመኘሁት ለኢትዮጵያ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ነው። ለኢትዮጵያን አዲስ ዓመት አዲስ የትምህርት ዘመን በሆኑ ነው። ተማሪና አስተማሪ ተነጣጥለው አይታዩም። መምህራንም ባሉበት ተማሪዎችም አሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በግብታዊነት ተነስተው  አስተማሪና ተማሪን ነጥለው ያቀርባሉ። አስተማሪው ሥራው ማስተማር ብቻ የሚመስላቸውም አልታጡም። መምህሩ ከተማሪው መማሩን ይዘነጉታል። የትምህርት ደረጃው ከፍ እያለ የዕውቀት አድማሱ እየሰፋ ሲሄድ መምህሩ የተማሪዎቹ ተማሪ እየሆነ ይሄዳል። ለመምህሩ  የዕውቀት ምንጭ ከልዩ ልዩ ሕብረተሰብና አካባቢ የሚመጣው ተማሪ ሊሆን ነው። አርዕስቴን ሳልቅ በአንድ ወቅት ከአንደኛ  ክፍል  ተማሪዬ የተማርኩትን እነሆ። በገጠር ትምህርት ቤት ነበር። ተማሪዎች አራት አምስት እየሆኑ  ወደትምህርት ቤት ይመጣሉ። አምስት ሆነው ከሚመጡት ውስጥ በአካልም በዕድሜም ይበላለጣሉ። አንደኛው በዕድሜው ከፍ ያለው ሌሎቹን ለምሳቸው ቋጥረው ካመጧት ቆሎ ላይ በጭብጥ  ያሰገብራቸዋል። ግብሩ ተደጋገመባቸው። ሰለዚህ ተሰብስበው ከሥራ መሪው ዘንድ ቀረቡ። የእኔ ክፍል ተማሪዎች ስለነበሩና ቋንቋን ስለምናገር ከተከሳሹ ጋራ ወደኔ ይዟቸው መጣ። ይህ ልጅ ርቦት እንደላደረገው እናውቃለን። የራሱ በቂው ነው።ቆሎው የገብስ ነበር። ምንአልባት ልዩነቱ ያንዳንዶቹ ሱፍ ወይም ሽንብራ ይኖረዋል። ዝርዝር ጉዳዩ ውስጥ አልገባንም። የተማሪን ሰም ፃፍኩና የነ እገሌን ቆሎ በመቀማቴ ወንጀል ሆኖብኝ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ላልቀማቸው በመልካም ጓደኝነት ልቀጥል ወድጄ ፈርሜአለሁ። የሚል አረፍተ ነገር ጽፌ  አቀረብኩለት።

‵ጋሼ′ አለኝ ወይ አልኩት። ‵አትዋሹ አላልከንም′ ‵አዎ ብያለሁ′  ‵ታዲያ እኮ ይህን ወረቀት ወድጄ አይደለም የምፈርመው ተገድጄ ነው′ ሲል  ሥራ መሪው ከወንበሩ ወርዶ በሣቅ ወለሉ ላይ ተፈራፈረ። ፊርማው ቀርቶ አስታርቀን አሰናበትናቸው። ወደተነሣሁበት ልመለስ፤ በዓለም ዙሪያ ሆነ  በሃገር  በትልልቅ የትምህርት ተቋማት ና ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ መምህራን እንዳሉ እናውቃለን። በውጭም በሃገርም ያሉ የኢትዮጵያ መምህራን ያልተሳካላቸው ናቸው በዬ በድፍረት መናገር እችላለሁ።

መሳካት ማለት ሦስት መኝታ ክፍል ያለው ቤት ገዝቶ ቆንጆ ሚስት አግብቶ ሁለት ልጆች መውለድ መሳካት ነው የምትሉ ካላችሁ ዜሮ ስጡኝ።እንዴት ማለት መልካም ነው።በደረጃው ክፍ እየተባለ ሲኬድ ዕውቀቱ ወደመምህራኑ የሚፈሰው ከተማሪዎቹ ነው። በውጭ ሃገር ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩት ኢትዮጵያውያን ለዚያ አልታደሉም። ምንም እንኳን የሚያስተምሩበት አካባቢ የፍትሕ እጦት  ያስተዳደር መዛባት የረሃብን ሰቆቃ የግለሰብ መብት መደፈር ማግና ካርታ ‘Magna Charta’ የሚለው ሰነድ በኢንግሊዝ ፓርላሜት እ ኤ አ 1215 ንገሱን ዮሐንስ ‘John’  የሕዝብ ተወካዮች በእርሱ ላይ ኃይል ሥልጣን ያረጋገጠ በመሆኑ ከዚያ ጊዜ ጀምሩ የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት አበቃለት። የምዕራቡ ዓለም ለ796 ዓመታት ሲወድቅ ሲነሰ በዚህ ጎዳና የተጓዘ ነው።የሰው ልጅ አእምሮ ፍትሕ በነገሠበት የቱን ያህል እንደሚበለጽግ ፍትሕ ከሌለ የቱን ያህል እንደሚቀጭጭ  ሃገራችን ጥሩ ምሳሌ ናት። የ796 ዓመት ገና አልጀመርነውም። ዛሬ የኢትዮጵያ ፓርላማ  መለስ ዜናዊን ቅንጅት ያቀረባችውን ሰባቱን ጥያቄዎችን እንዲቀበል  የሕዝብ ተመራጭነታቸውን ኃይላቸውን ቢያሳዩት ከ796 ዓመታት በፊት የጀመሩትን ጉዞ በጀመርነው ነበር። እንግዲህ የኢትዮጵያን መምህራን የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ይህን ዓይነት መብት ካለው ሕብረተሰብ የመጡትን ተማሪዎች ነው። ከአካባቢው ከዓለም ዙሪያ በየጊዜው አጠራቅመው በማስረጃ አስደግፈው በመጽሐፍ መልክ የቀረበላቸውን ነው የሚያስተምሩት። ምናልባት ከሺ አንድ ብዙ መሰናከሎችን አልፈው ያሉበት የበለጸገው ሃገር ያልደረሰበት አዲስ ነገር ሊያገኙ ይችላሉ። ያም ቢሆን ባለቤትነታቸውን አያረጋግጥላቸውም። ቢረጋገጥም  ለአስተማራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊያውሉት አይችሉም። እዚያ ዝርዝር ውስጥ አልገባም። ሆኖም ቁጭት የለም ማለት አልችልም። አንድ የተማረ ኢትዮጵያዊ  ዓለም ያለችበትን ደረጃ የተረዳ  ሃገሩ  አሁን ባለችበት ሁኔታ ለልጅ ልጆቹ ትቷት ቢያልፍ ምን ይሰማዋል?  የፖለቲካው ሁኔታ ካልተለወጠ ምን ይደረጋል? የሚሉ አሉ። መማር እኮ ለሃገር ማንኛውን መሰዕዋትነት ለመክፈል የተገባ ቃል ኮዳን ነው።

ለምሳሌ ሃገራችን በፋሽሽት ኢጣሊያ ስተወረር፤ ክብር ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ በፈረሳይ፣ ሐኪም ወርቅነህ በኢንግሊዝ፣ ዶክተር መላኩ ብዕያን በአሜሪካ ዘራዕይ ደረስ በሮማ አብዲሳ አጋ በኢጣሊያን በረሃ ምን ያደረጉ ነበር። ያወቀ የነቃ  ሲባል የሕብረተሰቡ ሕመም የሚሰማው ማለት  ነው። ኮሎኒሉና ጅንራሉ አቡኑና ቀሳውስቱም ሼኩንና ደረሳውን የተማሩ ናቸውና የወገን ሕመም ይሰማቸዋል? የ796 ዓመት ጉዞ እነርሱንም ይመለከታል።

የሃገር ቤቶቹስ መምህራንና ተማሪዎች በአሁኑ ጊዜ ምን ይጠበቅባቸዋል። አንድ ተማሪ ስለአካባቢው መጠየቅ ካልቻለ መምህሩም ለጥያቄው መልስ ከነፈገው የመማርና የማስተማሩ ሥራ አከተመለት።በኦሮመኛ ‵አደን ገለ ገበያቲ′  ገበያው ተበተነ፤ መሸጥም መግዛትም የለም ማለት ነው።

በጎንደር የሚማረውና የሚያስተምረው መምህር ወያኔ ለሱዳን ስለሰጠው መሬት ካልተነጋገረ፣ ለሕዝቡ ካላሳወቀ፤ የጂጂጋው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን ስለኦጋዴን የሰዎች መብት መጣስ ካልተቃወሙ፤ የባሐር ዳሩ ዩኒቨርሲቲ፣

ተማሪና መምህር ስለአባይ ግድብ ጆሮ ዳባ ልብስ ካለ፤ የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮችና ተማሪዎች ፣ ስለሕብረተሰቡ ሰቆቃና ረሃብ አሁንም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም እንዲነግሯቸው ከፈለጉ፤ የአዋሳው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን ስለመሬት ለባዕዳን መሸጥና የማዕድን መዘረፍ ከማስቆም ይልቅ ስለ ቁራንና መጽሐፍ ቁዱስ በማውራት ጊዜያቸውን የሚያሳልፍ ከሆኑ፤ የመቀሌው ዮኒቨርሲቲው መስፍን ኢንጅነርግ በደጃፉ ላይ በታጋዮች ደም የተገነባውን የአባርታይድን መንደር ሺቅብ እያየ የሚመፃደቅ ከሆነ፤ የኦሮሚያው አዳማው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን ወደትምህር ቤት ሳይሆን ለባርነት በዓመት ሰላሳ ሺ እህቶቹ ወደ አረብ ሃገር ሲላኩ ነግ በኔ በልጆቼ ካላሉና በዘር ፖለቲካ ጊዜን የሚሳልፉ ከሆነ የትምህርቱ ጉዳይ አበቃለት። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መምህራንና ተማሪዎች በዚህ በ2004 ዓ ም አዲስ የትምህርት ዘመን በነፃነት ዕውቀትን የምትገበዩበት ይሁን። ይህም ሊሆን የሚችለው ያለ ፍረሃትና መሸማቀቅ በልብ ሙሉነት ማሰብና ማድርግ ስትችሉ ብቻ ነው። በሕብረተሰባችሁ ፍትሕ የሕግ የበላይነት የገለሰቦች መብቶች የማወቅ የማሳወቅ ግዴታ አለባችሁ። በአጠቃላይ ተማሪና አስተማሪ የሕብረተሰቡ ልሳን፤ የደም ሥር የመፍትሄ ጓዳ የሃገር አለይታ ናችሁ። መልካም ዓመት ይሁንላችሁ።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca